

# አዲስ ዘመን ለሁላችን፤ እንኳን አደረሰን!

እንኳን አደረሳችሁ፣

እግዚአብሔርን ስለናንተ እየባረክሁ፣

በኢትዮጵያ ውሥጥ ላላችሁ፤

እንዲህ እላለሁ።

በመተማመን፣ ተባብራችሁ፤

እንኳንም በቃ! አላችሁ።

ላልበላችሁት እዳ መክፈል፤

አንፈልግም በማለት

ለቆማችሁና አንቀለበስም እያላችሁ፣

የኢትዮጵያን ባንዴራ ላነሳችሁ፤

በመዘመርም እልል! እልል! ላላችሁ።

ሰላምታዬ ይድረሳችሁ፣

እንኳንም በጤና ለአዲስ ዘመን አበቃችሁ።

ድግሞም፣ ለሰማዕታት

ታሪክ ለሚያስታውሳችሁ፣

ለግላችሁ ሳይሆን፣ ለቅን ፍርድ ብላችሁ፣

ለሁሉ ኢትዮጵያኖች፣ ለወገኖቻችሁ፤

በህዋሐት (በወያኔ) ጥይት ለተሰዋችሁ።

ይኸውና አወጅሁኝ፤

ምንጊዜም በፍቅር አስታውሳለሁኝ።

ዘማሪው እንዳለው፤

“ኢየሩሳሌም ሆይ፥

ብረሳሽ፥ ቀኜ ትርሳኝ።” (መዝሙረ ዳዊት 137:5)

ተባረኩ በመሰዋት፣

አስገኛችሁልን ሰላምና ነጻነት።

በናንተ መንፈስ፣

እኛ ኗሬወቹ ታድሰን፣

**ለመባባል በቃን፣ እንኳን አደረሰን፤**

**በአዲሱ ዘመንም**

**ተባብለናል ጤና ይሥጠን ለሁላችን።**

© ለምለም ፀጋው መስከረም 1, 2009

**ለኢትዮጵያ አዲስ ዘመን ይሁን!**